# ሁለተኛውን የኮቪድ-19 ክትባት መስጠትን ስለማሰብ

በመጋቢት ወር 2022 የበሽታ መለለከያ ማዕከል (CDC) የኮቪድ-19 የክትባት መመሪያዎችን አሻሽሏል። ይኸውም መሥፈርቱን ሊያሟሉ የሚችሉ እና በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ሰዎች ሁለተኛውን የማጎልበቻ ክትባት መውሰድ ይችላሉ የሚል ነው። ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መሥፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ ሁለተኛውን ክትባት በፈቃድዎ አሁኑኑ ማግኘት ይችላሉ። ክትባቱ የሚያስገኘውን ጥቅምም ሆነ ጉዳት አውቀው ክትባቱን መውሰድ ይችላሉ። የእርስዎን የጤንነት ሁኔታ የሚከታተለው የጤና ጣቢያ ስለ ክትባቱ ያለውን ሁኔታ ያስረዳዎታል። ሁለተኛውን የማጎልበቻ ክትባት ለመውሰድ የሚያስችሉ ጉዳዮች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፦

## ክትባቱን ለመውሰድ ብቁ ነዎት

እነዚህን ሦስት ነጥቦች ካሟሉ አሁኑኑ ሁለተኛውን የማጎልበቻ ክትባት ለመውሰድ ብቁ ነዎት፦

- ዕድሜዎ 50 እና ከዚያ በላይ ሆኖ የመጀመርያውን ማጎልበቻ ክትባት ከ4 ወራት በፊት ከወሰዱ
- ዕድሜዎ አሥራ-ሁለትና ከዚያ በላይ ሆኖ መካከለኛም ሆነ ከባድ በሽታን የመከላከል ዓቅም ከሌለዎትና የመጀመርያውን ማጎልበቻ ክትባት ከ4 ወራት በፊት ከወሰዱ
- ከ4 ወራት በፊት ጃንሰን ክትባትን ሁለት ጊዜ ከወሰዱ

## እርስዎ ወይም አብሮዎት የሚኖር ሰው ሕመም ላይ ናችሁ?

አንዳንድ ሁኔታዎች የኮቪድ-19 ሕመምን የከፋ ያደርጉታል። ከላይ እንደተገለጸው እርስዎ ለሁለተኛው የማጎልበቻ ክትባት ብቁ ከሆኑ እርስዎም ሆነ አብረው ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ ሰዎች መከተብ ይችላሉ፦

- መካከለኛም ሆነ ከባድ በሽታን የመከላከል ዓቅም ከሌለዎት
- በኮቪድ-19 ሕመም ክፉኛ ከተጎዱ
- በሥራዎትም ሆነ በአካባቢዎ እንዲሁም በጉዞም ሆነ ብዙዎች በተሰበሰቡበት ቦታ ተገኝተው ለኮቪድ-19 በሽታ መጋለጥ የሚችሉ ከሆነ
- ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ድረስ በኮቪድ-19 የተጠቃ አካባቢ የሚኖሩ ከሆነ
- አብሮዎት የሚኖረው ሰው ያልተከተበ ከሆነ

## መቆየት ይችላሉ?

ሁለተኛውን ማጎልበቻ ክትባት ለመውሰድ ብቁ ቢሆኑም የሚከተሉት ሁለት ነጥቦች እንዳይወስዱ ያደርግዎታል፦

- በባለፉት ሦስት ወራት ኮቪድ-19 ተይዘው ከሆነ
- በአሁን ሰዓት ሁለተኛውን ክትባት መውሰድ አስፈላጊ አይደለም ካሉና ይኽንን ክትባት መውሰድ የሚያስፈልገው በመከር (FALL) 2022 መሆኑን ካመኑ ወይም አዲስ የኮቪድ-19 ዝርያ ወደፊት ሲመጣ ለመከተብ ካሰቡ

## ሁለተኛውን ማጎልበቻ ክትባት የሚወስዱ ከሆ፦

- የኮቪድ-19 ማጎልበቻ ከወሰዱ ቢያንስ 4 ወራት መሙላቱን ያረጋግጡ
- ሁለተኛው ማጎልበቻ ክትባት ሞደርና ወይም ፋይዘር መሆኑን ልብ ይበሉ። ዕድሜያቸው ከ12 -17 ያሉ የሚወስዱት ፋይዘር ብቻ መሆኑን ይወቁ
- ደካማ የሆነ የበሽታ መከላከያ አቅም እንዳለዎት የሚያውቁት እርስዎ ነዎት። ስለዚህም ይኽን ማረጋገጫ ሌላ ሰነድ አያስፈልዎትም

የትርጉም ምንጭ የተገኘው፦


**CDC References and Resources:**

COVID-19 by County www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/your-health/covid-by-county.html

Interim Clinical Considerations for Use of COVID-19 Vaccines Currently Approved or Authorized in the United States: www.cdc.gov/vaccines/covid-19/clinical-considerations/interim-considerations-us.html

Interim COVID-19 Immunization Schedule for Ages 5 Years and Older: www.cdc.gov/vaccines/covid-19/downloads/COVID-19-immunization-schedule-ages-5yrs-older.pdf

People with Certain Medical Conditions www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/need-extra-precautions/people-with-medical-conditions.html

U.S. COVID-19 Vaccine Product Information: www.cdc.gov/vaccines/covid-19/info-by-product/index.html



TAKS Faith Community Health Program.
2601 Minnehaha Ave. MPLS, MN 55406

Translated by Abraham Solomon | Communication Specialist | 5abrahamsolomon@gmail.com | Tel. (612) 275-9418